# የሲሚንቶ ኢንዱስትሪው ትራንስፎርሜሽን

ስሜነህ 03/11/14

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ልዩ ሚና ያለው ኢንዱስትሪ ነው። ኮንስትራክሽን የማይገባበት የልማት ዘርፍ የለም ማለት ይቻላል። እንደ መንገድ፣ የባብር መስመር ወዘተ ያሉ መሰረተ-ልማቶች መዘርጋት ከተፈለገ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። እንደትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት ወዘተ ያሉ የማህበራዊ መሰረተ ልማት ተቋሞችን እናስፋፋ ከተባለ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ቁለፍ ተዋናይ ነው። ፋብሪካዎችን እናሰፋፋ ከተባለ ከፋብሪካዎች ግንባታ ውጪ ከ30 በመቶ እስከ 60 በመቶ የሚደርሰው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ድርሻ ነው። በከተማም ሆኖ በገጠርም የህዝቡን ኑሮ ማሻሻል ከተፈለገ አንዱ ገጽታው የመኖሪያ ቤቶችን መገንባት ነው፤ በመሆኑም በዚህ ረገድም ኮንስትራክሽን የላቀ ሚና ይጫወታል። በመሰረቱ የግንባታ ስራ ከፍተኛ ግብአትን የሚጠይቅ ስራ ነው። ለዚህ ደግሞ መፍትሄው የኮንስትራክሽኑን ዘርፍ ማሰደግነው ማለትም በየትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ፈጣን እድገት ለማምጣት ከተፈለገ ቀልጣፋና ጠንካራ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን መገንባት ያስፈለጋል። ስለሆነም ነው ለብዙ ኢንዱስትሪ ዘርፎች በር ከፋችና መነሻ ለሆነው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ላይ ልዩ ትኩረት የተሰጠው።

ይህ የሆነበት አቢይ ምክንያትም ሰፊ የሰው ሃይል የሚጠይቁትና ለበርካታ ዜጎችም ሰፊ የስራ እድል መፍጠር ለሚችሉት የቤት ልማትና የመንገድ ግንባታ ዘርፎች የተለየ ተኩረት የተሰጠው ከዚሁና ከሥራ ዕድል ጋር ከተያያዘው ትርፍ ባሻገርም ለዘርፉ ግብአት የሚሆኑ ኢንዱስትሪዎችን ይዘው ስለሚወጡና በዚሁ ግንባታ ሂደትና በሩ በሚከፈትባቸው ኢንዱስትሪዎችም ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስለሚኖር ነው።

ከፊል ዕድሜውን እያጠናቀቀ ያለው የ5 ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መቃኛውም ይኸው የኮንስትራክሽኑ ዘርፍ ነው። የሥራ እድል፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ቀለጣፉ የትራንስፖረት አገልገሎት፣ ቀለጣፉ የግብይት ስርዓትና የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ወዘተ አንዱ ለአንዱ መነሻና መወጣጫ እንዲሆንና ተመጋግበውና ተደጋግፊው የሚያድጉበትን ስርዓት በሚፈጥር መንገድ የተቃኘ ነው። በዚህም በየዘርፉ በርካታ ውጤቶች መመዝገባቸውን ባሳለፍናቸው ግማሽ የእቅድ ዘመኑ አመታት ብቻ ማየትና ተጠቃሚም መሆን ችለናል።

39 የሚደርሱ ልዑካንን የያዘውና በመንግስት የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት አስተባባሪነት የጉብኝት ጉዞ ያደረገው የጋዜጠኞች ቡድን በምስራቁ የሃገራችን ክፍል የ7 ቀን ቆይታ አድርጓል። እነዚህኑ ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ጋር የተያያዙና የእርሱ ውጤት የሆኑ ኢንዱስትሪዎችን ለመጎብኘት የተንቀሳቀሰው ቡድን ከተመለከታቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች መካከል ዘንዱ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከፍተኛ ግብአት እንደሆነ የሚታወቀው የሲሚንቶ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ነው። ይኸውም **የድሬደዋው ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ** ሲሆን በእርግጥም ፋብሪካው በእቅዱ ዘመን ለተያዙ በርካታ የመሰረተ ልማት ዘርፎች ግብዓት ከመሆኑም በላይ ለበርካታ ሰራተኞች የስራ ዕድል መፍጠሩንና ለቴክኖሎጂ ሽግግርም በር መክፈቱን አይተናል።

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ከተያዙትና በምስራቁ የሃገራችን ክፍል እየተደረጉ ካሉት የልማት እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ መዋእለ ነዋይ እንደፈሰሰበት የሚነገርለት በድሬደዋ የሚገኘው ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ነው። በቀን 70ቶን ብቻ እያመረተ ከ1936 እስከ 1998 ዓ.ም የዘለቀው ድሬደዋ ሲሚንቶ ፋብሪካ በ1998 ዓ.ም በ2.1 ቢሊዮን ብር ካፒታል ወደግል ይዞታነት ከተዘዋወረ በኋላ ከአንድ ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የሥራ እድል እንደፈጠረና የማምረት አቅሙንም በቀን ወደ 3 ሺህ ቶን ወይም 44 ሺህ ኩንታል ማድረስ መቻሉን ከቦታው ላይ ተገኝተን ማረጋገጥ ችለናል። በተለይ ቀድሞ የነበረውና ወደግል ይዞታነት የዞረው ነባሩ ፋብሪካ ከድሬደዋ መጠነ ሰፊ እድገት ጋር ተያይዞ ከዳር ወደ መሃል ሽግግር ማድረጉ የሚፈጥራቸውን የአካባቢ ብክለትና መሰል ችግሮች፣ በሌላ መልኩም

የማሽነሪውን እርጅናና ኋላቀርነት በመገንዘብ ይህንኑ ባማከለ መልኩ ነባሩን በአዲስ የመተካት ስራ በእቅድ ዘመኑ በመከናወኑ ዛሬ ላይ የደረሰው ይህ ፋብሪካ በቴክኖሎጂና መሰል ዘርፎች በእጅጉ ልቆና በልጽጎ በማምረት ሂደት ላይ ይገኛል።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የመንግስትን አቋምና ማበረታቻዎች እንዲሁም ድሬደዋ ለሲሚንቶ ምርት ዋና በሆነው ጥሬ እቃ ላይም ስቶን በስፋትና በቅርበት የሚገኝባት አካባቢ መሆኗን ታሳቢ በማድረግ የዛሬው ፋብሪካ እንደተቋቋመ የነገሩን የፋብሪካው የስራ ሃላፊዎች፤ ለፋብሪካው ግንባታ የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን ጨምሮ ዛሬም ምርት በማጓጓዝ ሂደት ላይ የሚገኙ እያንዳንዳቸው 40 ቶን የመጫን አቅም ያላቸው 90 ትራከሮች ከቀረጥ ነፃ መግባታቸውንም አውግተውናል።

የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀደም ከተለመደው አይነት በላይ የሆነ የታክስ የእፎይታ ጊዜ (ኤክስፖርት በሚያደርግ ጊዜ ቫት አለመክፈልንም ይጨምራል) የተሰጠው ይህ ፋብሪካ ከመንግስት ጋር ያለው ግንኙነት ከግንባታው በኋላም የቀጠለ እንደሆነ በሃላፊዎቹ በኩል ተነግሮናል። በተለይ በኤክስፖርት በኩል  የፕሮሞሽኑን ሥራ በመንግስት ሰፊ ድጋፍ እያከናወነ የሚገኘው ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ አሁን ባለበት ደረጃም የገበያ ችግር እንደማያሰጋው አረጋግጧል። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ አካባቢዎችን ገበያ ሙሉ ለሙሉ የያዘው ናሽናል ሲሚንቶ አሁን ደግሞ ወደ አዲስ አበባም መግባት ጀምሯል።

ከሁሉ የሚልቀውና ከመንግስት የተደረገለት ድጋፍ መገለጫ የሚሆነው ደግሞ የትራንስፎርሜሽን እቅዱ ዋና ማዕቀፍ ከሆነው የባቡር መስመር ግንባታ ውስጥ ከድሬደዋ እስከ ሚኤሶ ያለውን የሲሚንቶ ግብአት ይህ ፋብሪካ ብቻ እንዲያቀርብ መደረጉ ነው። ከዚህ ባሻገር በድሬደዋና በምስራቁ የሃገራችን ክፍል የሚደረጉ (ከአዳማ እስከ ኢትዮጵያ ሶማሌ) በሚገኙ ከተሞች የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሚከናወነው በናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ምርት ነው። ግና የአውሮፕላን ማረፊያና መሰል መሰረተ ልማቶች እንደሚገነቡ እቅዱ ላይ በመመላከቱ የገበያ ስጋት የለብንም ያሉት የሥራ ሃላፊዎች ይልቁንም በምስራቁ የአገሪቱ ክፍል የሲሚንቶ

ፍላጎት አሁን ካለው ፍላጎት እንደሚጨምር የሚያመለክት ጥናት እንዳለም አሜውተውናል።

ከተመረቀ አንድ አመት ከሁለት ወር ያስቆጠረው አዲሱ የድሬደዋ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ በአንድ አመት ብቻ 9.3 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ወደጅቡቲና ሶማሊያ ለመላክ ቢያቅድም ከብዙ ሃገራት የሚገቡ የሲሚንቶ ምርቶች የሃገራቱን ገበያ በርካሽ ዋጋ እንዳጥለቀለቁት ባደረጉት ጥናት ማረጋገጣቸውንም ሰምተናል።

ያም ሆኖ ግን ርካሽ ዋጋ ያላቸው የሲሚንቶ ውጤቶች የኤክስፖርት መዳረሻ በሆኑት ሃገራት መግባታቸው ተግዳሮት ቢሆንም በገበያ ህግጋት መሰረት ሳያዋጣም ገበያ ውስጥ መግባትና የናሽናል ሲሚንቶን ምርት ማስለመድ ተገቢና ከረዥም ጊዜ አኳያ ውጤት የሚኖረው በመሆኑ "እናደርገዋለን" በማለትም የፋብሪካው ሃላፊዎች አብራርተዋል።

ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል የተጠየቁት አንድ ከፍተኛ የስራ ሃላፊም የማምረቻ ዋጋን በመቀነስ እንደሚከናወን አስረድተዋል። ፋብሪካው ከሰው ሃይል ጀምሮ የማምረቻ ማሽነሪዎቹ ከፍተኛ ዋጋን የጠየቁ ሲሆን ከሰው ሃይልና ከቴክኒክ ጋር የተያያዘውን የኢትዮጵያውያኑን አቅም በመገንባትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር፤ አቅም ከተገነባና የሰው ሃይል ካበቃ በኋላ አሁን ካሉት የማምረቻ ማሽኖች አጅግ ዘመናዊና አነስተኛ ዋጋ ያላቸውን በማስገባት ነባሩን የመተካት፣ በሎጂስቲክስ አቅርቦት በኩል የነበረውን ችግር ከጅቡቲ ድሬደዋ እየተገነባ ያለው የባቡር መስመር ግንባታ ሲጠናቀቅ የሚቃለል ችግር በመሆኑ፤ በአነስተኛ የማምረቻ ዋጋ ርካሹን ገበያ መቆጣጠርና መወዳደር እንደሚቻልም አብራርተዋል። ከላይ በኢንዱሰትሪ ስትራቴጂው ላይ የተገለፀውም ሆነ በእቅዱ አግባብ አንዱ የአንደኛው ኢንዱስትሪ መነሻና መወጣጫ እንዲሆን የተመለከተው ንድፈ ሃሳብ በድሬደዋ ፋብሪካ መሬት ላይ መውረዱንም ከዚሁ የሃላፊው ገለፃ መረዳት ችለናል።

ከሲሚንቶ ገበያ ጋር ተያይዞ ለፋብሪካው የስራ ሃላፊዎች የቀረበላቸው ሌላም ጥያቄ ነበር። ይኸውም ለመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግብአት የሚሆኑ ምርቶችን

የሚያቀርበው ድሬደዋ ናሽናል ሲሚንቶ የመንግሰት ፕሮጀክቶች ቢቋረጡ ምን ይሆናል? ምንስ ተማምኖ ነው? የሚሉት ይገኛሉ። ታዲያ  የስራ ሃላፊዎቹ የሰጡት መልስ መልስ ብቻ ሳይሆን የስተራቴጂውንና የእቅዱን መሰረታዊ መርሆዎችና መነሻዎች ጠንቅቀው መገንዘባቸውንም የሚያመላክት ጭምር ነበር።

ሲሚንቶን በተመለከተ የመጀመሪያው ተጠቃሚ መንግስት እንደሆነ የገለፁት የስራ ሃላፊዎች አሁን ባለው ሁኔታ እና በሲሚንቶ ኮንስትራክሽን መለኪያ ህግ መሰረት ግንባታዎች እየተጀመሩ አንጂ ተሰርተዋል አይባልም። በዚህም የተነሳ ፍላጎቱ ገና ኢምንት ነው ብለውናል። ይልቁንም በእነዚህና አሁን በሚደረጉት የኮንስትራክሽንና መሰል የኢንዱስትሪ ግንባታ ሂደቶች ኢኮኖሚው አንደሚያድግና፤ ኢኮኖሚው ሲያድግ ደግሞ የህዝቡ የነፍስ ወከፍ ገቢ እንደሚያድግ፤ በዚያው ልክ ዜጋው የአኗኗር ዘይቤውን ለመለወጥ ስለሚፈልግ የሲሚንቶ ገበያ በእኛ ሃገር ሁኔታ ገና ያልተነካ መሆኑንም አብራርተውልናል። እንደውም  ስጋታቸው ወይም ችግራቸው ገበያው እንዳልሆነና  ይልቁንም ስጋታቸው  ወይም ችግራቸው የራሳቸውና የውስጥ እንደሆነ ያወሱት ሃላፊው ስጋታቸው ተወዳዳሪ ሆኖ የመገኘት ጉዳይ እና በአነስተኛ ዋጋ ማምረት የሚቻልበትን አቅም ከመፈጠር ጋር የተያያዘ እንደሆነ አውግተውናል። ሌላውን እንኳን ብንተወው፣ በሌሎች ሃራት እንደሚደረገው ሁሉ ወደፊት ሃገሪቱ ስታድግ የመንገድ ግንባታዎች ሁሉ በሲሚንቶ ኮንክሪት ስለሚገነቡ ገበያው ሰፊና ጥልቅ ይሆናል።

የሃላፊው መብራሪያ ይህ ብቻ አልነበረም፤ *ከባቡር መስመር ዝርጋታው ጋር ተያይዞ አሮጌው ፋብሪካ የሚሰራው ስራ እንዳለ ያረጋገጥን ሲሆን አዲሱ ፋብሪካ በምስራቁ የሃገራችን ክፍል ካለው ከፍተኛና የበላይ የሆነ የገበያ ድርሻ እንደተጠበቀ ሆኖ በጥቅሉና እንደሃገር የናሽናል ሲሚንቶ የገበያ ድርሻ ከ11-15* በመቶ መሆኑንም በስፋት ዘርዝረዋል።

ሃገራችን ከተያያዘችው የልማት እንቅስቃሴና የፀረ ድህነት ዘመቻ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሚነሳ አንድ ነገር አለ። የልማት ሂደቶች እና ዘመቻዎቸ ሁሉ ለአካባቢ ጥበቃ ተኩረት የነፈጉ የሚመስል ፍረጃ። ታዲያ ለድሬደዋ ናሽናል

ሲሚንቶ ፋብሪካ ሃላፊዎችም ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል አንዱ ይኸው ነበር። የፋብሪካው የኦፕሬሽን ዘርፍ ሃላፊ እንደገለፁልን የፋብሪካው የብናኝ (Dust) ልቀት 30 ሚሊግራም እንደሆነና ይህ ደግሞ በአለም አቀፍ መለኪያ መሰረት ደረጃውን የጠበቀና ዘመናዊ ፋብሪካዎች የሚባሉት የሚያሟሉት ነው። ፋብሪካው የማምረቻ ዋጋውን ለመቀነስ ከነደፋቸው ስትራቴጂዎች መካከልም አንዱ ይኸው ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዘው መንታ ትርፍ ነው። በአስተዳደሩ ከተማ የሚገኙ ከቡና ገለባና የጫት ገረባ እንዲሁም ሌሎች ቆሻሻዎችን በመሰብሰብ ከተማዋን ፅዱ ከማድረግ ባሻገር ቆሻሻውን ወደ ነዳጅ በመቀየር 60 በመቶ የማምረቻ ዋጋ መቀነስ የሚያስችለውን ተረፈ ምርቱን ወደ ባዮ ጋስ የመቀየር ጥናት ፋብሪካው እንዳጠናቀቀ ሃላፊው ነግረውናል።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በሚስፋፋበት ወቅት ኢንዱስትሪውን የሚመግቡ የተለያዩ ግብአቶችን የሚያቀርቡ ሌሎች ኢንዱስትሪዎችም አብረው እንደሚያድጉ ተገልጿል። በእነዚህ ዘርፎች መካከል ቀልጣፋ የግብይትና የመመጋገብ ስርዓት ከሌለ በአንድ በኩል የኮንስትራክሽን ኢንዱስሪ እድገት ለሌሎች ዘርፎች የሚፈጥርልንን የተጨማሪ እድገት እድል እንዳንጠቀም በማድረግ እድገታችን መሆን በሚገባው ደረጃ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሳይሆን እንዲቀር ያደርገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የደጋፊ ኢንዱስትሪዎቹ እድገት አብሮ መራመድ ባለመቻሉ የኮንስትራክሽን ሥራ ዋጋ እንዲንር፣ የስራ ጥራትም እንዲጓደል ብሎም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እድገት እራሱ እንዲዳከም ማድረጉ አይቀሬ ይሆናል። ስለሆነም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከተመጋጋቢ ሌሎች ዘርፎች ጋር ተደጋግፎና ተመጋግቦ ማደጉን ማረጋገጥ የእቅዱ ቁልፍ ነጥብ እንደሆነ በመግቢያዬ አካባቢ ተመልክቷል። ይህንኑ ተደጋጋፊነትና ተመጋጋቢነት ያለው የኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት ማስፈለጉንና መኖሩን ከድሬደዋ ናሽናል ማረጋገጥ ተችሏል፤ ፋብሪካው በትራንስፎረሜሽን ደረጃ ላይ እንደሆነ ማረጋገጡም እንደዛው።